DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

# የ ዲሲ ሄልዝ (DC HEALTH) የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች የቴሌ ሄልዝ//TELEHEALTH/ የሙከራ ፕሮግራም

የዲስትሪክት tኦፍ ኮሎምቢያ የጤና መምሪያ (DC Health) በቅርቡ የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች ፕሮግራምን (SHSP) ማስፋፋት ጀምሯል። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ  ውስጥ ጤናን፣ ድህንነትንና፣ እና ፍትሃዊነትን ለማሳደግ የDC Health ተልዕኮ ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች የ Telehealth ፕሮግራም (SHSTP) በመላው ዲስትሪክት በSHSP ውስጥ የሚሳተፉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች የtelehealth አገልግሎቶችን ያቀርባል። የጤና ቡድን ሰራተኞች በተማሪ ግምገማቸው መሰረት ለመጎብኘት ቴሌ ሄልዝ/telehealth/ ለመጠቀም ሊወስኑ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ ቺልድረን ናሺናል (Children’s National) እና ሌሎች አቅራቢዎች ጋር የ ቴሌ ሄልዝ//telehealth/ የምክር አገልግሎቶች ለህክምና ጉዳዮች መመሪያ እና ህክምና እንደ አስፈላጊነቱ ለትምህርት ቤት የእንክብካቤ ሰራተኞች ዝግጁ ይሆናል።

## ስለ ትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች የtelehealth ፕሮግራም በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች፦

### *የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች  ቴሌ ሄልዝ/telehealth/ ፕሮግራም ምንድን ነው?*

ፕሮግራሙ ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ሲሆን ተማሪዎችን ከህክምና አቅራቢዎች ጋር ለማገናኘት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለተማሪዎች ተደራሽነትን ይጨምራል። ኮምፒውተሮች፣ ታብሌቶች፣ ዌብካሞች እና በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ልጅዎ እና የ SHSTP አቅራቢው መገናኘት እንዲችሉ ስልኮች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም፣ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፣ እንደ ኤሌክትሮኒክስ ስቴቶስኮፕ የልብ ምትን ለማዳመጥ እና ካሜራ ያለው ኤሌክትሮኒክስ ኦቶስኮፕ የልጅዎ ጆሮ ውስጥ ለማየት የሚጠቅሙ ዓይነቶች።

### *የዚህ ፕሮግራም ጥቅሞች ምንድን ናቸው?*

በSHSTP በኩል፣ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና ፈጣን የህክምና ሁኔታዎች ምርመራ ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም፣ ፕሮግራሙ፥

- ለተማሪዎች ከትምህርት ቤት የሚርቁበትን ጊዜ እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ከስራ የሚያርፉበትን ጊዜ ይቀንሳል።
- ለህጻናት ህክምና የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢዎች ተደራሽነት ይጨምራል
- ተማሪዎች የተወሳሰቡ ወይም ስር የሰደዱ የጤና ሁኔታዎችን እንዲቆጣጠሩ ይረዳል።
- የስፖርት ጉዳት ቶሎ እንዲታወቅ ያደርጋል
- የመጓጓዣ ጊዜን እና ወጪዎችን ይቀንሳል

### *በቴሌ ሄልዝ/telehealth ጉብኝቱ የሚመራው ወይም የሚሳተፈው ማን ይሆናል?*

የትምህርት ቤት የጤና ቡድን ሰራተኞች የቴሌሄልዝ መሳሪያ ላይ ይሰራሉ። የህጻናት ህክምና SHSTP አቅራቢ በቪዲዮኮንፈሬንስ አማካኝነት ቀጠሮውን ያካሄዳል። በተጨማሪ፣ የተወሰኑ የጉብኝቱ ክፍሎች በቴሌሄልዝ አቅራቢ መመሪያ ስር በጤና ቡድን ሰራተኞች ሊደረጉ ይችላሉ። አቅራቢ የልጅዎን ጉብኝት ለመደገፍ ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን በማሳተፍ የእንክብካቤ ቅንጅት ውስጥ ሊሳተፍ ይችላል።

ሁለቱም የጤና ቡድን ሰራተኞች እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ሁሉንም የተገኘ መረጃ ሚስጥራዊነት ይጠብቃሉ። ወላጆች እና አሳዳጊዎች ለልጅዎ ጉብኝቶች ይጋበዛሉ፣ ይሁን እንጂ፣ እነርሱን ማግኘት ካልቻልን፣ ጉብኝቱ በታቀደው መሰረት ይቀጥላል።

### *የእኔ ተማሪ በቴሌ ሄልዝ /telehealth/ ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፍ ካልፈለኩስ?*

ማንኛውም ተማሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያለ ወላጆቻቸው/አሳዳጊያቸው ግልጽ የጽሁፍ ስምምነት በtelehealth ፕሮግራም ሊሳተፉ አይችሉም። መሳተፋቸው አስፈላጊ መሆኑ ለሚሰማቸው፣ ነገር ግን በፋይል የተጻፈ የወላጅ ስምምነት ለሌላቸው ተማሪዎች፣ ለአገልግሎቶች የቃል የወላጅ ይሁንታ/ስምምነት/ ሊሰጥ ይችላል። የቃል ስምምነት መጠቀም ድንገተኛ ላልሆኑ የህክምና ሁኔታዎች ለወላጆች የቀረበ የአንድ ጊዜ እርዳታ ነው። የመጀመሪያውን የ SHSTP ጉብኝት በኋላ፣ ወላጆች ለወደፊት ጉብኝቶች የጽሁፍ ስምምነት ማቅረብ ይጠብቅባቸዋል።

### *ምን ዓይነት አቅራቢዎች ይገኛሉ?*

የህጻናት ህክምና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች በህጻናት ብሄራዊ ሆስፒታል የሚሰሩ ሲሆኑ የ በቴሌ ሄልዝ /telehealth /ጉብኝት በሚያስፈልግበት ጊዜ ይገኛሉ። ወደፊት፣ ፕሮግራሙ ከሌሎች የጤና እንክብካቤ ድርጅቶች የተወጣጡ የህጻናት ህክምና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን ለማካተት ይስፋፋል። የ በቴሌ ሄልዝ /telehealth/ ጉብኝት ሲጀመር፣ ተማሪዎች አፋጣኝ አገልግሎትን ለማመቻቸት ቀጥሎ ወደሚገኘው የህጻናት ህክምና የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይመደባሉ። በአሁኑ ጊዜ፣ ተማሪዎች/አሳዳጊዎች ተመራጭ አቅራቢ የመምረጥ አቅም የላቸውም እናም ጉብኝቱን በተገኘው መሰረት ለማመቻቸት አንድ ሰው ይመደባል።

### *ከቴሌሄልዝ ጉብኝት የተሰበሰበ መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል?*

አቅራቢዎች በህግ ወይም በደንብ ስለሚፈለግ ወይም የልጅዎን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት፣ ልዩ የህክምና መረጃን ለትምህርት ቤት ባለስልጣናት እና ለዲሲ ሄልዝ/DC Health/ ሊለቁ ይችላሉ። የቪድዮ ክፍለ-ጊዜው አይቀዳም፣ ግን እንደ ፎቶዎች ያሉ የተወሰኑ ይዘቶች፣ አስፈላጊ ከሆነ፣ ለህክምና ግምገማ፣ ሊወሰዱ ይችላሉ። ቅጂዎቹ በሚስጥር ተይዘው ይቀመጣሉ።

የጤና ቡድን ሰራተኞች የጉብኝቱ መዝገቦችን፣ ለሁሉም የጤና ቡድን ጉብኝቶች እንደሚያደርጉት፣ በትምህርት ቤቱ የተማሪ የጤና መዝገብ ውስጥ የጉብኝቱን መዛግብት ይይዛሉ። እነዚህ ፋይሎች በይለፍ ቃል የተጠበቁ ናቸው እና ከህጻናት የትምህርት ቤት አገልግሎቶች እና የዲሲ ሄልዝ/ DC Health/ ሰራተኞች በስተቀር ለማንም ተደራሽ አይደሉም። ዲሲ ሄልዝ/DC Health/ እና CSS በፌደራል የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) መሰረት የተማሪዎችን የተጠበቀ የጤና መረጃ ግላዊነትን መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም የቴሌ ሄልዝ/ telehealth/ አገልግሎት አቅራቢው የተማሪውን ጉብኝት የህክምና መዝገብ ይይዛል። በተጨማሪ እነዚህ በጤና መድህን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (HIPAA) በሚጠይቀው መሰረት በሚስጥር ይጠበቃል።

### *የቴሌ ሄልዝ/telehealth/ ፕሮግራም ተደራሽነት በአላንት/እረፍቶችን ጨምሮ አመቱን ሙሉ ይሰጣል?*

የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎት የቴሌ ሄልዝ/ Telehealth /ፕሮግራም ተደራሽነት የሚቀርበው በመደበኛ የትምህርት ሰአታት የትምህርት ክፍለ ጊዜ እና የጤና ቡድን ሰራተኞች በሚኖሩበት ጊዜ ብቻ ነው። የቴሌ

ሄልዝ/Telehealth/ አገልግሎቶች በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት፣ ከመደበኛ የስራ ሰአታት በኋላ፣ ወይም በበአል/በታቀዱ እረፍቶች አይሰጡም።

### ***ሌላ ማወቅ ያለብኝ ሌላ ማንኛውም መረጃ አለ?***

እርስዎ እና ልጅዎ የቴሌ ሄልዝ/telehealth/ ጉብኝትን ለማቆም በማንኛውም ጊዜ የጤና ቡድን ሰራተኞችን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢን የመጠየቅ መብት አላችሁ።

### ***የጤና ቡድን ሰራተኞች አሁንም በትምህርት ቤት የጤና ቡድን ውስጥ ይገኛሉ?***

አዎ፣ የትምህርት ቤት የጤና ቡድን ሰራተኞች የአካላዊ እና የባህሪ ጤና ሪፈራል፣ ልዩ የጤና ፍላጎቶች ላላቸው ተማሪዎች የጤና እንክብካቤ እቅዶችን ማስፈጸም፣ አስገዳጅ ማጣሪያዎች፣ እና የህዝብ ጤና ጥንቃቄዎችን ማስፈጸምን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ሳይወሰን በአካል የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማቅረብን ይቀጥላሉ። በተጨማሪ፣ የጤና ቡድን ሰራተኞች የህመም እና ጉዳቶች፣ የመድሃኒት መቆጣጠር፣ እና የመጀመሪያ እርዳታን በልምምድ ደረጃ ውስጥ የአጭር-ጊዜ የህክምና ቁጥጥርን ይሰራሉ። ልጅዎ ተቀዳሚ የእንክብካቤ ሃኪም ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ካስፈለጋቸው፣ የጤና ቡድን ሰራተኞች የአቅራቢዎች ዝርዝር እንዲኖር ያደርጋሉ።

### ***በቴሌ ሄልዝ በኩል ለሚሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ እጠየቃለሁ?***

በመጀመሪያ፣ ታካሚዎች ለእነዚህ የ SHSTP አጣዳፊ የእንክብካቤ ጉብኝቶች ክፍያ አይጠየቁም፣ ይሁን እንጂ፣ የሂሳብ አከፋፈል ሂደት ወደፊት ሊተገበር ይችላል። የሂሳብ አከፋፈል ሂደት ከመጀመሩ በፊት፣ በ DC አነስተኛ የስምምነት ህጎች ውስጥ ከሚወድቁ አገልግሎቶች በስተቀር ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ከትምህርት ቤቶች የሚላክ መልዕክት ይኖራል። የክፍያ መጠየቂያ ሂደት ላይ ዝርዝሮች ሲጠናቀቁ የሚቀርቡ ይሆናል።

### **<u>የመገኛ መረጃ</u>**

ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ወይም ስለ ፕሮግራሙ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን በኢሜይል ይላኩ፡-

ዲሲ ሄልዝ/DC Health/ የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ፕሮግራም ኢሜይል
shs.program@dc.gov

አንድሪያ ጄ በውድሬዉክስ, PsyD, MPH, MA, FACHE
ዋና ዳይሬክተር
ቺልድረን ናሽናል ሆስፒታል
aboudreaux@childrensnational.org

በአማራጭ፣ የፕሮግራም ምርመራን በ DC Health የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎቶች ፕሮግራም ድረገጽ አማካኝነት በdchealth.force.com/studenthealthservices ማስገባት ይችላሉ።